# ንጥቀትና አርማጌዶ




"ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፤ መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፥ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ።" (ማቴ.24:29-31)

በጸረ ክርስቶስ አገዛዝ አለም ጨለማ የስቃይና የመከራ ዘመኗን በድንገት ከሰማይ በሚገለጠው ጌታ ኢየሱስ በአንድ ቀን ይለወጣል። ብርሃን፣መለከት፣መብረቅ፣የመሬት መንቀጥቀጥና የከዋክብት ብልጭታ በምድር ሁሉ ይታያል። ጌታ ኢየሱስ እግሮቹ በደብረ ዘይት ተራሮች ላይ ይቆማሉ። በአርማጌዶን ጦርነት ጊዜ ጸረ ክርስቶስ ከሰማይ በመላዕክቱ ታጅቦ በሚመጣው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከምድር ይደመሰሳል። የጸረ ክርስቶስና የሰራዊቱ መደምሰሻ ቦታ የመጊዶ ሸለቆ በእስራኤል አገር በሃይፋ ከተማ አቅራቢያ ነው። በዚህም የሰው ልጅ ግፈኛ አገዛዝ ከምድር ላይ አንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያከትምና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የነገስታት ንጉስና የጌቶች ጌታ ሆኖ ከቅዱሳን ሰራዊቱ ጋር ምድርን ይገዛታል። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር የሚገዛበት ጊዜ የሺህ አመት መንግስት ተብሎ ይጠራል። በዚህን ጊዜ ምድር ቀድሞ በኤደን ገነት የነበራት ውበትና ክብር ይመለስላታል፤ ሰላምም ለሺህ አመት ይሰፍናል።

ዝግጅት

እግዚአብሔር ከ6 ሺህ አመታት በላይ ለሰው ልጆች በመጨረሻው ዘመን ለሚሆነው ክስተት የዝግጅት ጊዜ ሰጥቷል። በተለይ የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ በምድር ላይ አሁን ሊገለጥ በደጅ እንዳለ ብዙ ምልክቶች ተገጣጥመው እያሳዩ ናቸው። የመጨረሻው ዘመን ብዙ የሰይጣን ማጭበርበርና ምድርም በኀይለኛ ክፋት የምትዋጥበት ዘመን ይሆናል። በዚህ ጊዜ ጸንቶ ለመቆም እንደነገሩ የሆነ ጸሎትና የአምስት ደቂቃ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ አያዋጣም። አባል ነኝ ለማለት ያህል ብቻ ቤ/ክ አባል መሆን በራሱ በቂ አይሆንም።

አሁን ያለንበት ዘመን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ነውጥ የበዛበት ነው። የጸሎት ትጋት፣ የጾም ትጋትና የቃሉ ትጋት ከወትሮ በላቀና በበዛ ሁኔታ ሊኖረን ይገባል አለበለዚያ ጌታ ከኛ ከሚጠብቀው ባነሰ የህይወት መሰጠት ለጌታ መምጣት የተዘጋጀን መሆን አንችልም። ከላይ የዘረዘርናቸውን ምልክቶች ስንመለከት የጌታ መምጣት በደጅ መሆኑን እንወቅ!

ዝግጅቶች፡-

1. በንሰሀ በኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ
2. ከኀጢአት በመራቅ በቅድስና መኖር
3. ቅዱስ ቃሉን በማንበብ የእግዚአብሔርን እውነት ማወቅ
4. በጾምና በጸሎት መትጋት
5. ቃሉን በመታዘዝ መኖር
6. በተሰጠን ጸጋ እግዚአብሔርን ማገልገል